# <u>አፍቃሪ ብርቱካኖችና ተናዳፊ ንቦች</u>

ፀሎተ-ሃሙስ የፈረንጆች ማርያም 2011

ሙሉነህ ዮሃንስ-ሲያትል ከተማ




ለስምንት ወራት ሙሉ በዝናብ ሲንዠቀዠቅ የነበረው የሲያትል ሰማይ ዳመናውን እየገለጠ በጉጉት ለምትጠበቀው አጭር የበጋ ፀሀይ የተመቻቸ ይመስላል። እኔም ጨቅላዋ ልጄን ከውድ ባለቤቴ ጋር ሆኜ ፀሃይ ለማሞቅ ባለኝ ጉጉት ጀንበር ሳትጠልቅ ወደቤቴ ለመድረስ የመኪና ወፈ ሰማይ ከወረረው የ Inter State 5 አገር አቋራጭ አውራ ጎዳና ውስጥ እንደተዋጥኩ የእጅ ስልኬ አቃጨለች። ዲሲ የሚኖረው ጓደኛየ ኢያሱ ጊዜ ሳያባክን "ፌዴሬሽኑ ውሳኔውን መልሶ አስተካከለ አለኝ"። ከፀሃይዋ ይልቅ ይህ ጉዳይ የውስጥ ሞቅታን ፈጠረልኝ። አዎን ብርቱካን ሚደቅሳ አትላንታ ከተማ በሚደረገው የ28ኛው የሰሜን አሜሪካ የስፓርትና የባህል ፌዴሬሽን የክብር እንግዳ መሆኗ በማያዳግም ሁኔታ ተረጋገጠ። ውድ አንባብያን ብርቱካን የክብር እንግዳ እንድትሆን በፌዴሬሽኑ ቦርድ አባላት የተመረጠችው ከእስር የተፈታች ሰሞን ቢሆንም፤ የፌዴሬሽኑ ስራ አስፈፃሚ በሆኑ የተወሰኑ ግለሰቦች ከህገ-ደንባቸው ባፈነገጠ አሰራር ምክንያት በጉጉት ሲናፍቃት ከነበረው ኢትዮጵያዊ ማህረሰብ ጋር የማትገናኝበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። አንባቢዎቼን ከወዲሁ ለማስገንዘብ የምወደው ይህ ጉዳይ ብዙ ቁስልን ስለነካካ ስሜቱን ገላጭ የሆኑ ጠንከር ያሉ ቃላትን ልጠቀም ግድ ብሎኛል።

የዚህ ፅሁፍ አላማም የብርቱካን ሚደቅሳ የክብር እንግድነት ግብዣ-ነፈጋና-ዳግሚያ ግብዥ ምስቅልቅል ለምን እንደተፈጠረ፤ የውጥረቱ ዋና ተዋናዮች እነማን እንደነበሩ(እንደሆኑ)፤ ጉዳዮ የሚመለከታቸው አብይ ተዋናዮች የሰጡትን አስተያየትን ዳስሸ፤ በመደምደሚያው ከፍል ደግሞ ይህ ጉዳይ ስለ ብርቱካን የመጀመሪያ የስደት ምዕራፍ ስላለው እንደምታ መላ ምቶች እሰነዝራለሁ።

## <u>አነሳስ</u>

ጥቅምት 17 2010 አትላንታ በተደረገው የፌዴሬሽኑ የቦርድ አባላት ስብሰባ ላይ ስራ አስፈፃሚ የሆኑ ሰዎች ከውጭ ተማክረው በመጡት መሰረት የዘንድሮው የክብር እንግዳ ተጋባዣችን አርቲስት ማህሙድ አህመድ ስለሆነ ይፅደቅና አጀንዳው ይዘጋ ሲሉ ሌላ እጩ አለን ያሉ የቦርድ አባላት ትኩረት ሳቡ። እጩ እንግዳዋ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ መሆኗ ሲገለፅ የመደነቅ-የመደሰት-የመደንገጥ ስሜት

በተሰብሳቢው መፍጠሩን በቦታው የነበሩ ይምሰክራሉ። በአላሙዲን ንዋይ አፍቃሪነታቸው የሚታሙት ስራ አስፈፃሚ አመራር ውስጥ ያሉ ግለሰቦች ቦክስ ቀረሽ ንትርክና ማስፈራሪያ ቢደረድሩም ረዥም ሰዓታት የቀጠለው ውዝግብ ለጊዜው የገላገለው በድምፅ ብልጫ የቦርድ አባላቱ ብርቱካን የክብር እንግዳ እንድትሆን በመወሰን ነበር። ያልጠበቁትን ውሳኔ የተጋረጡት የስራ አስፈፃሚ ስብሰባ መሪ ሰዎች ከነመለስ ዜናዊ የተቀዳ የሚመስል ስልት ተጠቀሙ። ድምፁን ሃይል በተቀላቀለበት ምጭበርበሪያ ተጠቅመው አስቀለበሱት። ይህን ውሳኔ ያስሻሩት የፌዴሬሽኑን ህገ-ደንብ በቀጥታ በመጣስ ነበር። ይሄን የተገነዘበው በአሜሪካና በድፍን አለም የተበተነ ኢትዮጵያዊ የፍትህ መጓደል ጠመንዣ ባነገቱ የኢጋዚ ጦር መጨፍለቁ እያንገበገበን እዚህ በነፃነት አገር አይደረግም ብሎ እልህ አስጨራሽ ፈርጅ ብዙ ትግል አድርጓል።

## <u>አፍቃሪ ብርቱካኖችና ተናዳፊ ንቦች</u>

በተፈጥሮና በተለምዶ ንቦች ከብርቱካን አበባም ሆነ ፍሬ ይቀስማሉ። የዘመኑ ንቦች ግን ማር ላሾች ናቸውና የብርቱካን ጠቀሜታ ስላልታያቸው ለጋ ፍሬዋን በመርዛቸው ጠቅጥቅው ሊያጥፏት ሰፍረውባታል። የፍሬዋ ፈላጊዋ በዛና ለዘር ተረፈች።

የተከበረችው ዳኛ ብርቱካን ከቅንጅት እስከ አንድነት በዘለቀው የፓለቲካው ህይወቷ የኢትዮጵያዊያንን ብቻ ሳይሆን የአለም አቀፉንም ማህበረሰብ ቀልብ ስባለች። የሰሜን አሜሪካው የኢትዮጵያውያን ስፓርት ፌዴሬሽን ቦርድ አባላት ከጥንስሱ ለክብር እንግድነት ያጫት ግን ሰፋ ባለ መመዘኛ መስፈርት እንደሆነ አጠንክረው ይናገራሉ። እንዲያውም ያላት የተቃዋሚነት ፓለቲካ ተሳትፎ አይደለም እሷን እንዲመርጡ ያነሳሳቸው። እነዚህ ወገኖች ቆፍጣናዋ ዳኛ ባሳየችው ሚዛናዊ ፍርድ አሰጣጥ፤ በሃገራችንም ሆነ በአፍሪካ ፋና ወጊ ሴት-ወጣት የመጀመሪያ ትልቅ የፓለቲካ ፓርቲ መሪ በመሆኗና በአለም አቀፍ ደረጃ ያገኘቻቸው በርካታ የሰብዓዊ መብት ተቆርቋሪነት ሽልማቶች የክብር እንግድነት እጩነቷን አጉልተውታል።

እዚህ ላይ አሌ የማይባለው ግን እጅግ የበዙት ኢትዮጵያውያን ለብርቱካን ያላቸው ክብር የመጣው ባሳየቻቸው ቆራጥ የፖለቲካ አቋሟና በጨቋኙ ስርዓት በደረሰባት ተከታታይ ከባድ ግፍ የተነሳ ነው። ክብር ለብርቱካን-ድምፃችን ይከበር ብለው የውስጥ ትግሉን በማስተባበር ግንባር ቀደም ሚና የተጫወቱት የዲ.ሲ. ቡድንና በቀድሞው የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት በነበሩት በዳዊት አጎናፍር በሚመራው ቡድኖች እንደሆነ ይጠቀሳል። ከዛ በገዘፈ ደግሞ ስደተኛው ህዝብ ይህን ጉዳይ ስራየ ብሎ በንቃት ተከታትሎ ለውጤት አብቅቶታል። “ብርቱካን ትፈታ!” የሚለውን ተቋም በመምራት አለም አቀፉን ትግል ሲያስተባብር የነበረው ግርማየ ግዛውና ብዙ ባልደረቦቹ ደግሞ በሚኖሩበት አትላንታ ከተማ ህዝቡን በመቀስቀስ አብይ ሚናን እንደተጫወቱ ይገለፃል። ተያያዥነት ያላቸው ከፍተኛ የሚዲያ ቅስቀሳ በኢትዮጵያ ነክ ድህረ-ገፆች፤ እንደ አዲስ ድምፅና የአሜሪካ ድምፅ በመሰሉ ሬዲዮኖችና ዘመን በወለዳቸው ፌስ-ቡክ መሰል መገናኛዎች ብርቱካንን ጋብዙልን የሚሉ ውትወታዎች ሳያቋርጡ ተኸጎድጉደዋል።

በተቃራኒው ያሉ ወገኖች ደግሞ አንድም ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ንክኪ እንዳላቸው በሰፊው የሚነገር ሲሆን፤ አንዳንዶቹ ደግሞ በግንዛቤ ማነስና በጓደኝነት ስሜት ተገፋፍተው እንደሆነ ይነገራል። በጥቅሉ ብርቱካን አትጋበዝ የሚሉት ሃይሎች ጉዳዮ ፌዴሬሽኑን ፓለቲካ ውስጥ ያስገባዋል፤ ህገ-ደንባችንን ይፃረራል፤ ህጋዊ ፍቃዳችንን ያስነጥቅብናል የሚሉ መከራከሪያዎችን ይሰነዝራሉ። የብርቱካን መጋበዝ አግባብነት የለውም ብለው አጥብቀው ሲከራከሩ ከቆዩት ውስጥ በግንባር

ቀደምትነት ከሚጠቅሱት አንዱ እያያ አረጋ ሲሆን የህዝብ ግንኙነቱ ፋሲል አበበ ደግሞ የልትሚያው ማህል ውስጥ ተሰንቅሯል።

እነዚህ ሁለት የለየላቸው ጎራዎች በየፊናቸው ስድስት ወራት የፈጀ ፈርጀ-ብዙ ትግል አርገው ኢትዮጵያውያን ስንናፍቀው የምንኖርለት የህግ የበላይነት እየተደበደበም ቢሆን በጠረጴዛ ውይይት እልባት አገኘ። አዎን የቦርድ አባላት በስራ አስፈፃሚው የተጋረጠባቸውን መሰናክል ሁሉ ተቋቁመው በሃሳብ ስትባዝን ከከረመቸው አትላንታ ከተማ ኤፕሪል 16 2011 በድጋሚ ለመሰብሰብ ቻሉ። ከከፍተኛ ክርክርም በኋላ፡-

1) ብርቱካን የክብር እንግዳ እንድትሆን የተሰጠው ድምፅ መቀልበስ ህገ-ደንባቸውን መፃረሩን አምነው የቀደመው ውሳኔ እንዲተገበር በሙሉ ድምፅ ተስማምተዋል።
2) በተያያዘም ሌላው የክብር እንግዳ እጩ ተደርጎ የቀረበዉ አርቲስት ማህሙድ አህመድም በተደራቢነት የክብር እንግዳ እንዲሆን ተስማምተዋል።
3) በሶስተኛነት የወሰኑት ደግሞ በስራ አስፈፃሚነት ያሉት ሰዎች የስልጣን ጊዜያቸው ወደማለቁ ስለሆነ የስራ ልምድ እየቀሰሙ ሽግግሩን የሚሞሉ አሁንም በተደራቢነት ከተሰናባቹ ስራ አስፈፃሚው ቡድን ጋር ሆነው የፌዴሬሽኑን ስራ እንዲያስተባብሩ አምስት የተመደቡ መሆኑን ከቦርድ አባላት ተረድተናል።

## ስለውሳኔው ሰዎች ምን ይላሉ?

ስለፌዴሬሽኑ አዲስ ውሳኔ ለጉዳዮ ቅርበት ያላቸውን አካላት አነጋግሬ ነበር። በቅድሚያ ያነጋገርኩት የፌዴሬሽኑ የቀድሞ ፕሬዚዳንት የነበረውን ባሁኑ ደግም ክለቡን ወክሉ የቦርድ አባል የሆነውን ዳዊት አጎናፍርን ነበር። ዳዊት የብርቱካን መጋበዝ እውን እንዲሆን ረዥም ርቀት ተጉዟል። አትላንታ ድረስ ተጉዞ ትልቅ ትኩረት የሳበ ህዝባዊ ውይይት አስደርጓል። እሱ እንደሚለው ለመርህ ለመገዛት ነው። ዳዊት በውጤቱ መደሰቱን ጠቅሶ ፌዴሬሽኑ ስህተቶቹን እያረመ ያድግ ዘንድ ቅርብ የህዝብ ድጋፍ ስለማስፈለጉ አስረገጦ ይገልፃል።

ተደናቂው የአዲስ ድምፅ አዘጋጅ አበበ በለው ጉዳዮን በቅርበትና በጥልቀት ከዘገቡት መካከል ግንባር ቀደም ነው። ውሳኔው አንድ አራተኛ እርምጃ መሆኑን አስምሮ ፌዴሬሽኑ ብዙ ማፅዳት ያለበት ገመናዎች እንዳሉበት ገልጿል። ይሁንና ይህ ጥፋትን አምኖ መቀብልና ማረም ሊበረታታ የሚገባ ጅምር መሆኑን እያስገነዘበ የተለየኝ ስጋቱን አጋርቶኝ ነው። ፌዴሬሽኑ የፈጠረው አላስፈላጊ ውዝግብ ብዙ ሰው እቅድ አርጎ ከመሄድ አስተጓጉሉ ሊሆን ይችላል ብሏል። የአትላንታ ኗሪ የሆነው ግርማየ ግዛው ግን ኢትዮጵያዊው በውሳኔው ስለሚደስት ወደ ከተማችን መጥታችሁ በጉጉት ከምንጠብቃቸው የክብር እንግዶች ጋር አብረን እንስንብት ቤት አሙቀን እንጠብቃለን በማለት ወገናዊ ግብዥ አስተላልፏል። የደመደመው ግን ፌዴሬሽኑ ጥገና ሳይሆን ቀጣይ መሰረታዊ ለውጥ እንደሚያስፈልገው ገልፆ ነው።

በተደጋጋሚ ፈጣን ምላሽ ስለሰጠኝ በቅድሚያ የማመሰገነው የፌዴሬሽኑ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ ፋሲል አበበ ፌዴሬሽኑ በሰራው ስህተት በግሉም ሆነ በድርጅቱ ስም ህዝቡን ታላቅ ይቅርታ ጠይቆ፤ ስህተታችንን አምነን እርምት እርምጃ መውሰዳችን አበረታች ጅምር ነው ይላል። ፋሲል እንደገለፀው ውሳኔውን እንድናስተካክል ከሁሉም በላይ ያስገደደን የህዝቡ ጥያቄ ነው ብሎ የአሰራር ግድፈት

እንደነበረም አምነንበታል ብሏል። በአደራነት የተወው መልክትም ይህ በረዥም አመታት የተገነባ ተቋም ይበልጥ እንዲያድግ ገንቢ የህዝብ ተሳትፎ እንደሚያስፈልገው አስምሮ ነው።

## ብርቱካን ትገኝ ይሆን?

እዚህ ላይ አንድ አግባብ ጥያቄ ማንሳት ግድ ይላል። ብርቱካን ስለግብዥው ምን ትል ይሆን? ትቀበልን ወይስ ልረፍብት ትል ይሆን? ለዚህ ሪፖርት መልስ አገኝ ዘንድ ያደረኩት ሙከራ ባይሳካልኝም፤ ውዝግቡ የተጀመረ ሰሞን ከወ/ሪት ብርቱካን ባደረኩት የስልክ ልውውጥ እንደተረዳሁት ጉዳዮ አግራሞት እንደፈጠረባትና በቅርብ እንደምትከታተለው ነው። ጉዳዮን ከፍ እናድርገውና የብርቱካን የፓለቲካ ቀጣይነት ለምንድነው እንደተደበሰበሰ ያለው? ለምንስ ከሚዲያ ራቀች? ለሚናፍቃት ህዝቧስ ምነው ቃላት አጠሯት?

የብርቱካን አትላንታ ከተማ መሄድና አለመሄድ የታዳሚውን ህዝብ ብዛት ጠቋሚ ብቻ ሳይሆን የርሷንም የፖለቲካ ጉዞ አመልካች ሊሆን ይችላል። ለአዘጋጁም ሆነ ለህዝቡ ግን ውለታዋን የምትመልሰው ያልዘገየ መልስ ስትሰጥ ነው ቢባል አግባብነት አለው። ብርቱካን ብቻ ሳይሆን ህዝቡም አይዞህ ባይ ፈላጊ ባይተዋር ነውና!